# የ2007 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀምና ውጤት እንዲሁም የማዕድን ዘርፍ የመጀመሪያው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን (2003-2007) ዕቅድ አፈፃፀም

## 1. መግቢያ

የመንግሥት ዋነኛ የልማት አጀንዳ ድህነትን መቀነስና በሂደትም በማስወገድ ሀገራችን ረጅም በማይባልበት ጊዜ ወስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ እንድትሰለፍ እና በሂደትም የበለጸጉ ሀገሮች የደረሱበት ደረጃ እንድትደርስ ማድረግ ነው፡፡ ይህንንም እውን ለማድረግ የሚያስችሉ የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችንና ፕሮግራሞች ተነድፈው ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ተከናውነዋል፡፡ ባለፉት አምስት (2003-2007) የልማት ዕቅድ ዓመታት በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማቶች ፈጣን ዕድገት በማምጣት ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ከፍተኛ ወጤት ተመዝግቧል፡፡ ይህ ዕድገት አገራችን የተጋረጠበትን የከፋ ድህነት ለመቀነስ ብሎም ደረጃ በደረጃ ለማስወገድ የሚቻል መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡

ሀገራችን እያስመዘገበች ያለውን የኢኮኖሚ ዕድገት ቀጣይነት ለሚጋገጥና መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለማሰለፍ የተቀረጸወን ራዕይ ዕወን ለማድረግ ከ2003 እስከ 2007 ድረስ ያለውን ጊዜ የሚሸፍነው ሀገራዊ የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተዘጋጅቶ ለተግባራዊነቱ ከፍተኛ ርብርብ ተደርጓል፡፡

ባለፉት አምስት የልማት ዕቅዱ ዘመን በተለይ በ2007 በጀት ዓመት የማዕድን ዘርፍ የትኩረት አቅጣጫ የነበረው ለኢንቨስትመንት አጋዥና ምቹ የሆኑ የፖሊሲና የህግ ማዕቀፎችን በማውጣት ልማቱን የማስተዳደርና የመቆጣጠር፣ የማዕድናት ልማት ቦታዎችን እንዲሁም የሰራተኛውንም ሆነ የልማት አካባቢውን ህብረተሰብ ጤንነትና ደህንነት የማጠበቅ፣ የግሉ ዘርፍ በማዕድናት ጥናትና ልማት እንዲሰማራ ለማድረግ የሚያስችሉ ማስረታዊ የጂኦሳይንስ ሚጃዎችን አሰባስቦ ለተጠቃሚዎች የማቅረብና ዝርዝር የማዕድን ፍለጋና ጥናት እንቅስቃሴ ተጠናክሮ እንዲቀጥል በማድረግ ሀገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ እንድትሰለፍ የዘርፉን ልማት የማፋጠን ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡

በመሆኑም በልማት ዕቅዱ የትግበራ ዘመን በተደረገው እንቅስቃሴ የውጭ ምንዛሪን ከማስገኘት እና አዳዲስ የማዕድን አለኝታ ቦታዎችን ከማለየት እንዲሁም መሠረታዊ የሥነ ምድር ሚጃዎች ከማሰብሰብ አኳያ አበረታች ወጤቶች ተገኝተዋል፡፡

በአጠቃላይ የዘርፉ የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም የተገኘው ወጤት አበረታች ሲሆን ይህ የዘርፍ ወጤት ሀገራችንን ወደ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለማሰለፍ በመንግስት የተቀማጠውን ሀገራዊ ራዕይ እንደሚያግዝ ይታመናል፡፡ በመሆኑም የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ የ2007 በጀት ዓመት አበይት ተግባራት አፈፃፀምና ወጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 2. የ2007 በጀት ዓመት የአብይ ተግባራት አፈፃፀምና ወጤት

### 2.1 የማስፈጸም አቅም ግንባታ ፕሮግራም አፈፃፀምና ወጤት

- የሥራ ክፍሎችን የመልካም አስተዳደር ዕቅድ አፈፃጸም በመከታተል እና በማምገም የጽሁፍ ግብረ መልስ በማስጠት ድጋፍ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በመልካም አስተዳደር ዕቅድ ላይ **ከከፍተኛ** አመራሩ፤

**ከመካከለኛ አመራሩ፣ ከፈፃሚው፣ ከተገልጋዮችና እና ከባለድርሻ አካላት** ጋር ወይይት **በማድረግ የተገኙ ግብዓቶችን** ለቀጣይ ስራ **በመጠቀም ውጤታማ** ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡

- ከተገልጋዩች/ከደንበኞች ጋር የምክክር መድረክ እንዲካሄዱ ማድረግ በተጨማሪም በብሮሸር፣ በመጽሔት፣በደህረ ገጾች፣ በማስታወቂያ ሰሌዳ ወዘተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶች እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡
- የሚኒስቴር መ/ቤቱን የሥራ ክፍሎች የስራ አፈጻጸም ወጤት ተኮር ስርዓት /BSC/ ማለኪያ ማስፈርት ማስረት በመማዘን የላቀ ወጤት ላስማዘገቡ ፈጻሚዎች የሚበረታቱበት ሥርዓት ተፈጥሯል፡፡
- የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጭ ይሆናሉ ተብሎ የሚገመቱ የተለዩ እና በቀጣይ የሚለዩ አሰራሮችን መፍትሄ የማስቀመጥ እና የማምማም ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡
- የአማለካከት፣ የዕወቀት እና የክህሎት ክፍተቶችን እንዲሁም (ከሀይማኖት፣ ከብሔር፣ ከቋንቋ፣ ከቡድንተኝነት፣ወዘተ..) የሆኑ የስራ ማነቆዎች ለማታገል ስልጠናዎች በማዘጋጀት ለሰራተኛው ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ተሰርቷል፡፡
- የሥራ ክፍሎችን አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻልና ለደንበኞች ቅሬታ አፋጣኝ ምላሽ አሰጣጥ ሂደትን ለማሻሻል በBPR እና በዜጎች ቻርተር ማስረት አገልግሎት ማስጠታቸወን ማከታተልና ግብረ መልስ የማስጠት ስራ ተሰርቷል፡፡
- ለወጠን በዕወቀትና በክህሎት ለማምራት እንዲቻል ፖኬጆች ላይ የአጭር ጊዜ የአማለካከት ስልጠናዎች እንዲሰጡ ለማድረግ ታቅዶ ለ9 ወንድ እና ለ11 ሴት በድምሩ ለ20 አዳዲስ ፈጻሚዎች በለወጥ መሳሪያዎች ላይ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በማስፈጸም አቅም ግንባታው ወይም በመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ፕሮግራሙ ትግበራ ላይ ከተለያዩ ተቋማት የሚገኙ ተሞክሮዎችን በመቀመር ወደ ተቋማችን የማስፋት ስራ ተሰርቷል፡፡
- **የመካከለኛ አመራሩ ልማቱን ለማፋጠንና መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ የተቀረጹ የሪፎርም ፕሮግራሞችን ውጤታማ ለማድረግ በሙሉ አቅሙ ለመንቀሳቀስ ስልጠና የወሰዱ ሲሆን** በአማለካከት፣ በክህሎትና በዕወቀት ለማበቃት አጫጭር ስልጠናዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በየደረጃው ተሰጥቷል፡፡

- ለአዲስ ቅጥር ሠራተኞች በተቋሙ አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ ዙሪያ ከተለያዩ የሥራ ክፍሎች በተውጣጡ ኃላፊዎችና ከውጭ በተጋበዙ ባለሙያዎች ለ10 ቀናት በተሰጠው ስልጠና ላይ ግንዛቤ እንዲጨበጡ የተደረገ ሲሆን አንዳንድ የተሳሳተ የአሟካከት ተግዳሮት ያላቸውን ፈጻሚዎች ለማስተካከል ጥረት ተደርጓል፡፡
- በለውጥ ሰራዊት የተደራጁ ቡድኖች በቃለ-ጉባኤ የተደገፈ ሳምንታዊ ውይይት እያደረጉ ግንባር ቀደሞችን በማየት፣ የእርስ በእርስ በመማር፣ ያጋጠሙ ችግሮችን በማየት የመፍትሔ አቅጣጫ በማስቀመጥ የተሻለ ሥራ ተሰርቷል፡፡

## 2.2 የስነ- ምድር መረጃ ጥራትና ሽፋንን ማሳደግና የማዕድን ፍለጋ ፕሮግራም አፈጻጸምና ውጤት

በዚህ ፕሮግራም ሥር ለማዕድን ፍለጋና ለመሠረተ ልማት ማስፋፋት ከፍተኛ ድርሻ ያላቸውን መሠረታዊ የጂኦሳይንስ መረጃዎች የማሰባሰብ፣ የማደራጀትና የማሰራጨት እንዲሁም ለአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችና ለኮንስትራክሽን ግብዓት የሚሆኑ ልዩ ልዩ ማዕድናት ፍለጋና ጥናት ሥራዎች በዕቅድ ተይዘው ተሰርተዋል፡፡ እንዲሁም ወህ አጠር ለሆኑ አካባቢዎች ቅድሚያ በመስጠት የከርሰ-ምድር ውሃ ፍለጋና ጥናቶች የተካሄዱ ሲሆን የኮር ድሪሊንግና ጂኦቴክኒክ ጥናቶች፣ የናሙና ምርመራ አገልግሎቶች፣ የጂኦተርማል ጥናት፣ የጂኦሳይንስ ላቦራቶሪ ማዕከል የማጠናከር፣ ለማዕድናት መገኛ አመቺነት ባላቸው አካባቢዎች የሪሞት ሴንሲንግና ጂአይኤስ፣ በጂኦሎጂና በጂኦኬሚስትሪ መረጃ መገኛነት አለኝታ ቦታዎችን የመምረጥ እና መረጃዎችን የማዘጋጀት ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ በአጠቃላይ የ2007 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርቧል፡፡

### 2.2.1 የጂኦሎጂካል ካርታ ዝግጅትና የግራቪቲ ጥናት፡-

**በ1:250,000 መስፈርት የሃገሪቱን የጂኦሎጂ ካርታ ሽፋን በ2006 ከነበረበት** 74.4% □□ 100% **ለማሳ□ፅ ታቅዶ** 82.4% **ማድረስ ተችሏል**፡፡ ይህ ክንውን ከ2006 በጀት ዓመት ክንውን አንፃር ሲታይ አፈፃጸሙ በ10.75% ጭማሪ አሳይቷል፡፡ይህንንም ግብ ለማሳካት 90,000 ካሬ ኪሎ ሜትር በሚሸፍን ቦታ ላይ የጂኦሎጂ እና የጂኦኬሚስትሪ መረጃዎች በማስከ ተሰብስቧል፡፡ እንዲሁም **በ1:500,000 መስፈርት በግራቪቲ ጥናት የሃገሪቱን** ሽፋን **በ2006 ከነበረበት** 98% □□ 100% ለ**ማሳ□ፅ** ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት ተከናውኗል፡፡

### 2.2.2 የጂኦኬሚትሪና የማዕድን አለኝታ ካርታ ዝግጅት፡ -

**በ**1:100,000 ***መስፈርት የጂኦኬሚስትሪና የማዕድን*** አለኝታ ካርታ **በማዘጋጀት** ቦታዎችን (Anomalous Areas) ***ለይቶ ለቀጣይ ዝርዝር ሥራ ዝግጁ ማድረግ*** **በ**2007 **በ**ጀት ***ዓመት*** 4% ***ለማ□ረስ ታቅ□*** ግቡን ቀድሞ በ2006 በጀት ዓመት ማካካት ተችሏል፡፡

### 2.2.3 የኃይድሮ ጂኦሎጂና የከርሰ ምድር ጥናት፡ -

***የሀገሪቱን የሀይድሮጂኦሎጂ*** ካርታ **በ**1:250,000 ***መስፈርት ሽፋን*** **በ**2006 ***ከነበረበት*** 70.6% □□ 83.7% ***ለማሳ□ፅ ታቅ□*** 78.6% ሜድረስ የተቻለ ሲሆን ከ2006 በጀት ዓመት አንፃር ሲታይ አፈፃጸሙ በ11.33% ጭማሪ አሳይቷል:: ይህንንም ግብ ለማካካት 90,000 ካ.ኪ.ሜ በሚሸፍን ቦታ የሀይድሮጂኦሎጂ ሚጃ ማስባሰብና ካርታ ሥራ በማከ ተከናውኗል፡፡ እንዲሁም ***ዝርዝር የከርሰ-ም□ር ውሀ ሀብት ጥናት*** **በ**2006 ***ከነበረበት*** 27,400 ካ.ኪ.ሜ □□ 30,400 ካ.ኪ.ሜ ለማድረግ ታቅዶ ከዕቅድ በላይ 36,400 ካ.ኪ.ሜ ተከናውኗል፡፡ ይህንንም ግብ ለማካካት 9,000 ካሬ ኪሎ ሜትር በሚሸፍን ቦታ ላይ በማከ ዝርዝር የጂኦፊዚክስ ጥናትን ባካተተ ሜሉኩ የከርሰ ምድር ውሃ ጥናት ተከናውኗል፡፡

### 2.2.4 የጂኦሃዛርድ ጥናት፡ -

**በ**1:250,000 ***መስፈርት የአገሪቱን የጂኦሃዛርድ*** (Geo-hazard) ***ጥናት ሽፋን*** **በ**2006 ***ከነበረበት*** 25.6% □□ ***27.1% ለማሳ□ፅ*** ታቅዶ 28.6% ሜድረስ የተቻለ ሲሆን ከንውኑ ከ2006 በጀት ዓመት አንፃር ሲታይ አፈፃጸሙ በ11.72% ጭማሪ አሳይቷል:: ይህንንም ግብ ለማካካት 33,084 ካ.ኪ.ሜ በሚሸፍን ቦታ ላይ በማከ የኢንጂነሪንግ ጂኦሎጂ ካርታና 23 ጣቢያ VES እንዲሁም 23 መ.ኪ.ሜ ማግኔቲክስ ተከናውነዋል፡፡

በተሚጡ አካባቢዎች የሜሬት መንሸራተት ዝርዝር ጥናት በ2006 ከነበረበት በቁጥር 12 ወደ 17 ለማድረግ ታቅዶ በቁጥር 14 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ ከ2006 ***በጀት ዓመት*** አፈጻጸም አኳያ ሲታይ በ16.67% ጭማሪ አሳይቷል፡፡ ይህንን ግብ ለማካካት 2,187 ካ.ኪ.ሜ የማከ ሚጃ ማስባሰብ ተከናውኗል፡፡

### 2.2.5 የኢንዱስትሪ ማዕድናት ጥናት፡ -

**በአገሪቱ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች ዝርዝር የኢንዱስትሪ ማዕድናት ፍለጋና ክምችት ግምት ከ**1:50,000 ***መስ□ርትና*** **በላይ** ***ማካሄድ*** **በ**2006 ***ከነበረበት*** 68 አለኝታ ቦታዎች ***ወደ 77 ከፍ ለማ□ረፅ*** ታቅዶ 73 ሜድረስ የተቻለ ***ሲሆን*** አፈጻጸሙ ከ2006 ***በጀት ዓመት*** አፈጻጸም ***አንፃር*** ሲታይ በ7.35% ጭማሪ አሳይቷል::

**ይህንን ግብ** ለማካካት በ1፡10,000-1፡2,000 ማስፈርት 50 ካ.ኪ.ሜ የጂኦሎጂ ካርታ፣ በቁጥር 125 የተለያዩ ናሙናዎች የማሰብሰብ እንዲሁም በሰው ሃይል ዝርግ ጉድጓድ ቁፋሮ 169 መ.ሜ ተከናወኗል፡፡ በዚህም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን ቆቃ አካባቢ 5 የካኦሊን አለኝታ ቦታዎች በጥናት ተከልለዋል፡፡

**2.2.6 የሜታሊክስ ሜድናት ጥናት፡ -**

**በአገሪቱ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች ዝርዝር** የሜታሊክስ **ማዕድናት ፍለጋና ክምችት ግምት ከ**1:2,000-1:5,000 **መስፈርት በማካሄድ በ**2006 **ከነበረበት** 56 አለኝታ ቦታዎች **ወደ 63 ከፍ ለማ□ረፅ** ታቅዶ ወደ 62 ማክደግ የተቻለ ሲሆን ከ2006 በጀት ዓመት አንፃር ሲታይ አፈፃጸሙ በ10.7% ጭማሪ አሳይቷል፡፡

**ይህንን ግብ** ለማካካት በቁጥር 700 የተለያዩ የጂኦኬሚስትሪና ፕሮስፔክቲንግ ናሙናዎች የማሰብሰብ እንዲሁም 750 መ.ኪ.ሜ የዝርግ ጉድጓድ/ፒት ቁፋሮ እንዲሁም 15 መ.ኪ.ሜ የቅየሳ ሥራ ተከናወኗል፡፡ በዚህም ስድስት የደለል ወርቅ አለኝታ ቦታዎች በኦሮሚያ ክልል 3 (ወልጌ መዳኖ፣ ለጋ ቡርቃና ዶጎ ሲዳሞ) እና 3 በቤኒሻንጉል-ጉምዝ ክልል (ሺርቆሌ፣ ስኖርና ባንጋ) ተከልለዋል፡፡

**2.2.7 የጂኦተርሚል ጥናት፡ -**

**ቅድመ ጥልቅ የፍለጋ ጉድጓድ ቁፋሮ የጂኦተርማል ዝርዝር ጥናት የተጠናቀቀባቸውን** ቦታዎች **ሽፋን በ**1:20,000 **መስፈርት በ**2006 **ከነበረበት** 36.4% □□ **68.2% ለማሳ□ፅ** ታቅዶ ወደ 45% ለማክደግ የተቻለ ሲሆን ክንወኑ ከ2006 በጀት ዓመት አንፃር ሲታይ አፈፃጸሙ በ23.6% ጭማሪ አሳይቷል፡፡ ይህንን ግብ ለማካካት አሉቶ 2 (ፊንቅሎ)፣ አሉቶ 3 (ቦቤሳ)፣ ናዝሬት (ቦኩ)፣ ዳሎል፣ ቦይና፣ ዳናብ፣ ዳሜሌ፣ ቦሴቲ፣ ኮኔ፣ ጠዶ፣ ዳሎል ዝርዝር የስትራክቸራል ጂኦሎጂና ሃይድሮተርሚል አልተሬሽን ጥናት **3,**000 ካ.ኪ.ሜ፣ በ**ተንዳሆ (ዱብቲ)** አይሮቤራና አላሎቤዳ፣ በዶፋን ፈንታሌና መተካ፣ ገደምሳ አሉቶ 2 ፊንቅሎ፣ አሉቶ 3 (ቦቤሳ) ቦሴቲ ናዝሬት (ቦኩ)፣ አራቢ፣ ዳሎል፣ ቦይና፣ ኮኔ 200 ስቴሽን የMTና የTEM ሰርቬይ እንዲሁም አሉቶ 2 ፊንቅሎ፣ አሉቶ 3 (ቦቤሳ)፣ ቦሴቲ፣ ናዝሬት (ቦኩ)፣ አራቢ፣ ዳሎል፣ ቦይና፣ ኮኔ 400 ስቴሽን የግራቪቲና የማግኔቲክስ ሰርቬይ ተከናወኗል፡፡

**በአሉቶ ላንጋኖ** 40 MWe **የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት የሚችል የ□ኦተርማል □□ልቅ □□ጃ□ እንፋሎት □ፅ□ ማ□ረፅ በ**2006 **ከነበረበት** 28.5% □□ **100%** ለማክደግ ታቅዶ 75% ሜድረስ ተችሏል፡፡ ይህንን ግብ ለማካካት 1,920 ሜትር የጂኦተርሚል ጉድጓድ ቁፋሮ የተከናወነ ሲሆን ከተቆፈረው ጉድጓድ በተገኘው **እንፋሎት** ላይ discharge Test ተደርጎ ውጤታማ ማሆኑ ተረጋግጧል፡፡

እንዲሁም □ኮር፣ የወሃና የጂኦተርሚል ጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ በ2006 ከነበረበት 2,958.25 ሜትር ወደ 16,000 ሜትር የኮር፣ ድሪሊንግ፣ ወደ 7,500 ሜትር የወሃ ድሪሊንግ እንዲሁም ወደ 20,000 ሜትር የጂኦተርሚል ጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ በዓመት ለማሳደግ ታቅዶ የኮርና ጂኦቴክኒክ **ድሪሊንግ** 1,371.55 ሜትር ፣የወሃ ድሪሊንግ 173 ሜትር እንዲሁም የጂኦተርሚል ጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ 1,920 ሜትር ተከናውኗል፡፡ አፈፃፀሙ ዝቅ ሊል የቻለው ተጨማሪ የኮር ድሪሊንግ ስራዎች ጥያቄ ከውጭ ባለመቅረቡ፣ አዲስ የወሃ መቆፈሪያ ሪግ ርክክብ ለሚጸም ጊዜ በመወሰዱ እንዲሁም የጂኦተርሚል ቁፋሮ ለማካሄድ የሚያወጣ የወሃ ፓምፕ ግዥ በተፈለገው ፍጥነት መሠረት ባለመከናወኑ ምክንያት ነው፡፡

## 2.2.8 የናሙና ምርመራና የጂኦሳይንስ ፕሮሞሽን ሥራ -

**የናሙና ምርመራን በ2006 ከነበረበት በዓመት** 34,972 ናሙናዎች □□ **45,**000 **ናሙናዎች ምርመራ ለማሳ□ዕ** ታቅዶ 36,065(የዕቅዱን 80.14%) **ናሙናዎች መመርመር ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅ ያለው** በመሳሪያ ብልሽት እና በሰው ኃይል ዕጥረት እንዲሁም በአንዳንድ ምርመራዎች ላይ ናሙና ባለመቅረቡ ምክንያት ነው፡፡ ይህንንም ግብ ለማካካት 21,498 የጂኦኬሚካል፣ 1,575 የወሃ፣ 627 የሀይድሮካርቦን፣ 2,775 የሚነራሎጂ/ፔትሮግራፊ፣ 874 የፊዚካል እና 8,716 የወርቅ ባር የናሙና ምርመራዎች ተከናውነዋል፡፡

የጂኦሳይንስ ላብራቶሪ ማእከል የISO/17025 ዕውቅና ለማግኘት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ለማሟላት ታቅዶ በሰው ኃይል እጥረት ምክንያት ችግሮቹ ሙሉ ለሙሉ ባለመቀረፋቸው70% ተከናውኗል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በሲቪል ሰርቪስ ሚ/ር አዲስ የላብራቶሪ አደረጃጀት እንዲሁም ተጨማሪ መደቦች ተፈቅዶ የባለሙያ ድልድል በማድረግ ወደ ስራ የተገባ በመሆኑ በቀጣይ ዕውቅናን ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፡፡ እንዲሁም □□ **ሰርቬዩ የመረጃ ማዕከል ያልገቡ የጂኦሳይንስ መረጃዎችን ማሰባሰብና ማደራጀት** በ2006 በጀት ዓመት ከነበረበት በቁ□ር **75** ወደ 80 ለማሳደግ ታቅዶ 85 የጂኦሳይንስ ሚጃዎች ተሰብስበው በማደራጀት ወደ ሚጃ ቋት ገብተዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ በሀገሪቱ የተሰበሰቡ **የጂኦሳይንስ** ሚጃዎችን መሠረት የሀገሪቱን የማዕድናት አለኝታ ቦታዎች እንዲተዋወቁ ለማድረግ 8 **የፕሮሞሽን ዶክመንቶችን** ለ**ማዘጋጀት** ታቅዶ 6 **የፕሮሞሽን ዶክመንቶችን** (የፖታሽ፣ የኒከል፣ የጂኦሃዛርድ፣ የኦፓል፣ የማንጋኔዝና የሸክላ አፈር) ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 3,000 የጂኦሳይንስ ሚጃዎችን ለተገልጋይ ለማሰራጨት ታቅዶ 4180 ተከናውኗል፡፡

የጂኦሳይንስ ሚጃን በዳታ ቤዝ በማያዝ በድረ-ገፅ ለተገልጋዮች ሚልቀቅ በ2006 ከነበረበት በቁጥር 4000 ወደ 5000 ከፍ ለማድረግ ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት ሚጃው በዳታ ቤዝ የማከገባት ሥራ የተከናወነ ሲሆን በድረ-ገፅ ለማልቀቅ ፖሊሲ እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡

## 2.3 የማዕድን እና የፔትሮሊየም ኢንቨስትመንትን የማስፋፋት ፕሮግራም አፈጻጸምና ውጤት

የማዕድን ሀብት ለሀገር ልማትና ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው የሚታወቅ ሲሆን ይህን አላቂ የህዝብና የመንግስት ሀብት ተገቢው ጥበቃ የሚያስፈልገውና ለህዝብ ጥቅምም በአግባቡ መዋሉን ሚረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም የዘርፉ ልማት በዘላቂ ልማት ላይ ተመስርቶ እንዲተገበር ተከታታይ የፖሊሲና የህግ ማዕቀፎችን በማውጣት የሀገሪቱን የማዕድንና የፔትሮሊየም ሀብት የሚስተዋወቅና አመቺ የኢንቨስትመንት አሜራጮችን የመፍጠር ሥራ ተከናወኗል፡፡

በልማት ዕቅዱ ዘመን በተቀመጠው የማዕድንና የፔትሮሊም ኢንቨስትመንት የማስፋፋት ፕሮግራም መሰረት በበጀት ዓመቱ የማዕድን ኢንቨስትመንትን መጠን በ2006 ከነበረበት 30.871 ቢሊዮን ብር ወደ 33.424 ቢሊዮን ብር ከፍ ለማድረግ ታቅዶ ወደ 32.592 ቢሊዮን ብር ለማሳደግ ተችሏል፡፡ እንዲሁም የፔትሮሊየም ኢንቨስትመንትን በ2006 ከነበረበት 363.28 ሚሊየን ዶላር ወደ 538.7 ለማሳደግ ታቅዶ ወደ 436.18 ሚሊየን ዶላር ማሳደግ ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ በቁጥር 70 የማዕድን ፍለጋና ምርመራ እንደዚሁም 5 የምርት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ በቁጥር 24 የማዕድን ፍለጋና ምርመራ እንዲሁም በቁጥር 7 የምርት ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን በበጀት ዓመቱ በድምሩ 31 ፈቃዶች ተሰጥተዋል፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅ ሊል የቻለው ነባር ፈቃድ አሰጣጥ በመቀየሩና ምርጥ ኩባንያዎችን ብቻ ለይቶ ወደ ዘርፉ ለማስገባት አዲስ የፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ በማውጣት ወደ ተግባር በማ ባቱ ነው፡፡

እንዲሁም በበጀት ዓመቱ በፔትሮሊየም ፍለጋና ልማት ለሚሰማሩ ባለሃብቶች 4 የፔትሮሊየም ሥራዎች ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 2 ፈቃዶች(የዕቅዱን 50%) ተሰጥቷል፡፡ በዚህም ከGBP ETHIOPIA RESOURCES B.V. ከተባለ የሩሲያ ኩባንያ ገዋኔ አል ወሃ በመባል የሚታወቀው በአፋር ክልል ውስጥ የሚገኘው 42,226 ካ.ኪ.ሜ ሥፋት ያለወን ቦታ እንዲሁም ከDELONEX ENERGY ETHIOPIA LIMITED ኩባንያ በኦጋዴን ውስጥ ብሎክ 18,19 እና 21 ጋር የነዳጅ ፍለጋና ልማት ክፍፍል ስምምነት በሚ/ር መ/ቤታችን እና በኩባንያዎቹ መካከል የፊርማ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል፡፡ በተጨማሪም ኒውኤጅ ኩባንያ የነዳጅ ፍለጋና ምርት ክፍፍል የፈቃድ ማራዘሚያ ስምምነት ለሚኒስትሩ አካል ለማቅረብ ዝግጅቱ ተጠናቋል፡፡

በ2007 በጀት ዓመት ከልዩ ልዩ የማዕድን ስራዎች ብር 387.913 ሚሊዮን ገቢ ለማሰብሰብ ታቅዶ ብር 152.79 ሚሊዮን (የዕቅዱን 39.3%) ለማሰብሰብ የተቻለ ሲሆን የተሰበሰበው ልዩ ልዩ ገቢ ከዕቅድ በታች ሊሆን የቻለው ልማታዊ ከባንያዎችን ብቻ ለይቶ ወደ ዘርፉ ለማስገባት አዲስ የፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ በመውጣቱ ምክንያት የማዕድን ፍለጋና ምርመራ ፈቃድ የማሰጠት ስራ መቀነሱ እንዲሁም በኩባንያዎች በኩል በማሽን ብልሽት፣ የኤሌክትሪክ ሃይል ዕጥረትና ፣ የክረምት ወራት ለምርት ምቹ ባለመሆን ምክንያት ምርት በመቀነሱ ከሮያሊቲ የሚገኘው ገቢ ከታቀደው በታች በመሆኑ ነው፡፡ በተመሳሳይ ከፔትሮሊየም ሥራዎች 4.33 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማሰብሰብ ታቅዶ 4.04 ሚሊዮን (የዕቅዱን 93.3%) የአሜሪካን ዶላር ገቢ ሊሰበሰብ ችሏል፡፡

እንዲሁም ከመሬት ኪራይ፣ ከሥልጠና፣ ከፊርማ ቦነስና ከነዳጅ ሥራዎች ጋር በተያያዘ መገባት ያለበት ገቢ ማሰብሰቡን በመከታተልና በመቆጣጠር በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ለማድረግ ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት ተከናውኗል፡፡ ወደ ውጭ ለመላክ ለሚቀርቡ 450 ኢኮኖሚያዊ ማዕድናት ጥያቄዎች ድጋፍ ለማሰጠት ታቅዶ በቁጥር 282 ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡

በበጀት ዓመቱ በኩባንያዎች አማካኝነት 5,421 ኪ.ግ ወርቅ፣ 207.97 ቶን ታንታለም እና 42,126 ሜ.ኩብ ዕምነበረድ ለብሔራዊ ባንክና ለውጭ ገበያ እንዲቀርብ ድጋፍ በማድረግ 261.704 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ታቅዶ በሚድሮክ ወርቅ አክስዮን ማህበር የተመረተ 3,505.146 ኪ.ግ ወርቅ፣ በኢትዮጵያ ማዕድን ሀብት ልማት አክስዮን ማህበር የተመረተ 90.80 ቶን ታንታለም እንዲሁም በተለያዩ ከባንያዎች የተመረቱ 506.05 ሜ.ኩ ዕምነበረድ ማዕድናት ወደ ወጪ እንዲላክ ድጋፍ ተደርጎ 114.93 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ተገኝቷል፡፡

## 2.4 የባህላዊ ማዕድናት ምርትና ግብይት ፕሮግራም

የባህላዊ ማዕድናት ምርትና ግብይት እንቅስቃሴ ህጋዊ ማእቀፍ ተከትሎ እንዲሰራ በመደረጉ በኮንድሮባንድ መልክ ወደ ጎረቤት አገሮች እየተሸጠ ሲባክን የነበረው የማዕድን ሀብት ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገትና በዘርፉ ለተሰማሩ ወገኖች ጉልህ ጠቀሜታ በማስጠት ላይ የሚገኝ ሲሆን ለወጠቱም መገኘት ዋናው ምክንያት አምራቾቹም ሆኑ አዘዋዋሪዎቹ በህግና በፕሮግራም ተደግፈው በተደራጁ የህብረት ሥራ ማህበራት እንዲንቀሳቀሱ በመደረጉና የሚመለከታቸውን አካላትን ማስተባበር በመቻሉ ነው፡፡
በመሆኑም በባህላዊ መንገድ ተመርቶ ለብሔራዊ ባንክና ለውጭ ገበያ ከሚቀርቡ የማዕድናት ምርቶች የተሻለ የውጭ ምንዛሬ ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡ በዚህም በዘርፉ ለተሰማሩ በርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር የባህላዊ ማዕድናት አምራቾች እና አዘዋዋሪዎች ዋና ተጠቃሚዎች ሆነዋል፡፡ በበጀት ዓመቱ በባህላዊ ማዕድን አምራች ክልሎች 100 ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲደራጁ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 86473 ሴት 45036 በድምሩ 131,509 አባላት ያሏቸው 98 ኢንተርፕራይዞች የተቋቋሙ ሲሆን ይህም በልማት ዕቅዱ ዘመን ቀደም ሲል የተቋቋሙትን ጨምሮ የባህላዊ ማዕድናት የህብረት ሥራ ማህበራትና የጥቃቅንና ልዩ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር 436 መድረሱን ያመለክታል፡፡
በ2007 በጀት ዓመት 546 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚያወጣ 14,000 ኪ.ግ ወርቅ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲቀርብ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 210.98 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚያወጣ 5,548.38 ኪ.ግ ወርቅ ብሄራዊ ባንክ ሊገባ ችሏል፡፡ ክንውኑ በ2006 በጀት ዓመት ከቀረበው 7,599.69 ኪ.ግ የወርቅ አፈጻጸም ጋር ሲነፃፀር በ27% ቅናሽ አሳይቷል፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅ ሊል የቻለው በተለያዩ ክልሎች የወርቅ አዘዋዋሪዎችን ግብር የማስከፈል ሥራ ተጠናክሮ በዚህ ዓመት በመጀመሩ የወርቅ አዘዋዋሪዎች ግብር ላለመክፈል እና መረጃ እንዳይገኝ ወደ ብሔራዊ ባንክ ወርቅ ማስገባት መቀነሳቸው፣ በዓለም ገበያ ወርቅ ከነበረበት በአውንስ(ounce) 1,600 ዶላር ወደ 1,100-

1,200 ዶላር በመቀነሱ የአምራቹ ቁጥር መቀነስና ምርቱ አነስተኛ መሆኑ እንዲሁም የህገ-ወጥ ንግድና ኮንትሮባንድ የቁጥጥር ሥራዎች በተፈለገው ደረጃ ተጠናክሮ በቅንጅት ባለማከራቱ ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በበጀት ዓመቱ 11,050 ኪ.ግ የጌጣጌጥ ማዕድናት ለዓለም ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 16.296 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚያወጣ 4,372.95 ኪ.ግ ጥሬ ኦፓል፣ 194.528 ኪ.ግ እሴት የተጨመረበት ኦፓል እንዲሁም 62,235.26 ኪ.ግ ከኦፓል ዉጪ በደምሩ 66,802.738 ኪ.ግ የጌጣጌጥ ማዕድናት ለውጭ ገበያ ቀርቧል፡፡ ከንወኑ ከ2006 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በመጠን በ32,482.406 ኪ.ግ ብልጫ ያለው ሲሆን በውጭ ምንዛሪ ግኝትም የ2.172 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ብልጫ አሳይቷል፡፡

የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ከዕቅድ በላይ ሊሆን የቻለው የሚቻቻያ ሥርዓት በመፍጠር የጌጣጌጥ የውጭ ንግድ በማስፋፋት ከወርቅ የታጣውን የውጭ ምንዛሪ ለማካካስና ዘርፉን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ታቅዶ በማከራቱ ነው፡፡

እንዲሁም በበጀት ዓመቱ 3.5 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚያወጣ 56.99 ቶን ታንታለም እና 22,000 ዶላር የሚያወጣ 3.88 ኪ.ግ ፕላቲኒየም ለውጭ ገበያ ቀርቧል፡፡

በአጠቃላይ በኩባንያዎችና በባህላዊ ማዕድናት አምራቾች ተመርተው ለብሔራዊ ባንክና ለውጭ ገበያ ከቀረቡ ማዕድናት ሽያጭ በበጀት ዓመቱ 345.73 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ተችሏል፡፡ የተገኘው የውጭ ምንዛሪ በ2006 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከተገኘው 514.5 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ጋር ሲነጻጸር ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ምክንያት በ168.77 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ቅናሽ አሳይቷል፡፡

በዘርፉ ያለውን የኮንትሮባንድ ችግሮች ለመቀነስ በሁሉም ክልሎች /ገቢዎች፣ የጸጥታ አካላትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት/ ጋር በጋራ በመስራት የኮንትሮባንድ ማስሚሮችን የማለየት ስራ ተከናዉኗል፡፡ በዚህም ከፌደራል የኮንትሮባንድ ቁጥጥርና ክትትል ግብረ-ኃይል ጋር በጋራ በመሆን በዘርፉ የሚታዩትን ህገ-ወጥ ዝውውር ለማስቀምና የክልል አመራሮች ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩ ለማድረግ በማዕድን ሚኒስቴር ህገ-ወጥ ግብይት ክትትል የሚያደርግ ግብረ-ኃይል ተቋቁሞ ዕቅድ አውጥቶ በጋራ ከፌደራል ግብረ ኃይሉ ጋር እንዲንቀሳቀስ ተደርጓል፡፡

## 2.5 የማዕድን ዘርፍ የምርምርና ሥርፀት ፕሮግራም አፈፃፀም ውጤት

በዚህ ፕሮግራም ሥር በሀገሪቱና በተ□ቃሚ ባለድርሻ አካላትን ፍላጐት ላይ በመመርኮ□ በጂኦሳይንስ ዘርፍ የምርምር ጥያቄዎችን/ችግሮችን መሰብሰብ፣ መለየትና በተመረጡት ላይ የምርምር ፅንሰ ሀሳብ በመቅረጽ የምርምር ሥራን በቅንጅት መስራት፣ በዘርፉ አዳዲስ የአሰራር ዘዴዎችን ማላመድና መፍጠር፣ ጠቃሚ ቴክኖሎጂዎችን እና የምርምር ውጤቶችን መለየት ወጤቶቹንም በስልጠና ማሸ□□ር እና ማስረ□ እንዲሁም በዘርፉ የሚከናወኑትን ጥናቶች በምርምርና ተስማሚ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ታግዘው ልማትን እንዲያማጡ ማድረግ ስራዎች የታቀዱ ሲሆን በ2007 በጀት ዓመት የተከናወኑ ስራዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ከክልል ማዕድን ቢሮዎች ጋር በመተባበር በማከ ለምርምር የሚዱ 200 ኪ.ግ የዳያቶማዮት ናሙዎችን ለማብሰብ ታቅዶ 150(የዕቅዱን 75%) ኪ.ግ ለማብሰብ ተችሏል፡፡

የማከ ናሙ መሠረታዊ የላብራቶሪ ፍተሻ ሲካሄድ በምግብና ማጠጥ ላይ ሚዛማኝ ለጠፍ ጎጂ የሆኑ ማዕድናትን የማየት፣ በዩኒቨርስቲዎች የድህረ ምረቃ ጥናት በተለይ በኬሚካል፣ ፊዚካልና ሌሎች ባህርያት ላይ ጥናት ሲደረግ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ስራ ተከናወኗል፡፡ በዚህም በቤንቶናይት ጥናትና ምርምር በሚማከት የሚዘጋጀው ሪፖርት 85% የደረሰ ሲሆን ከኢትዮጵያ የሸክላ ፋብሪካ ጋር በማሆን በብሎኬት ስራ ላይ የሲሚዮን ማጠን በመቀነስና በቤንቶናይት የመተካት እና ከማክዶ እንጨት የሚገኘውን ኃይል በድንጋይ ከሰል በማካካበት ሁኔታ ላይ ከሚማከታቸው ጋር ወይይት በማድረግ በቅንጅት ስለሚሰራበት ሁኔታ ላይ ስምምነት ተደርሷል፡፡

በተለያዩ ሚዲያዎች የምርምርና ጥናት ወጤቶችን ማስራጨት እንደዚሁም ተሞክሮዎችን መቀመር በቁጥር 1 ለማከናወን ታቅዶ በዕቅዱ ማስረት የተከናወነ ሲሆን በዚህም በአዲሱ የኦፓል ዓይነት የተዘጋጀው የመጀመሪያ ደረጃ ጥናት ወጤትን ማስረት በማድረግ በአለም አቀፍ የጀም ጆርናል ኒወስ "New Deposits of Black Opal from Ethiopia" በሚል ርዕስ በማታተም ለአገራችን አዲስ ብራንድ በማሆን አስተዋወቋል፡፡

ምርታማነት የሚያሻሽሉትን የአቅርቦት ወጪ መተንተንና ማመት በቁጥር 5 ጊዜ ለማከናወን ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት የተከናወነ ሲሆን በዚህም የዋጋ ስሌት ስራ ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪም ተስማሚ ምርጥ ተሞክሮዎችንና ቴክኖሎጂዎችን ማየት እና ማሚጥ በቁጥር 5 ጊዜ ተከናወኗል፡፡

## 2.6 የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች (Cross Cutting Issues) ፕሮግራም አፈጻጸምና ውጤት

ሚኒስቴር መ/ቤታችን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ዋና አካል አድርጎ የሚዝገብራቸው የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች የአካባቢ ጥበቃና የማህበረሰብ ልማት፣የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች እንዲሁም የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጉዳዮች ሲሆኑ እነዚህን ጉዳዮች በቅርበት የሚከታተሉ የስራ ክፍሎች በመ/ቤቱ እንዲደራጁና በሰው ኃይል እንዲጠናከሩ በማድረግ ሥራው በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

የአካባቢ እንክብካቤ ለዘላቂ ልማትና ለአረንጓዴ የኢኮኖሚ ዕድገታችን ወሳኝ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን በነባርና አዳዲስ የማዕድንና የፔትሮሊየም የልማት ሥራዎች ምክንያት በአካባቢ ላይ የሚደርሱ አሉታዊ ተፅኖዎች በአግባቡ መተዳደራቸውን፣ የተፈጥሮ ሃብት የማጠበቅና ከተጎዳም ተመልሰው እንዲያገግሙ መደረጋቸውን፣ የልማት ሥራዎች በሚከሄዱባቸው አካባቢዎች የማህበረሰብ ልማት ማካሄዱን ሚረጋገጥ፣ ባለፈቃዶች ለማህበረሰብ ልማት በጀት ለመመደብ በገቡት ወል መሠረት እየተንቀሳቀሱ መሆኑን የማከታተልና

የመቆጣጠር ሥራዎች  እንዲሁም የዘርፉ ልማት ከአየር ንብረት ለወጥ ጋር ተጣጥሞ መካሄዱን የማምገም ተግባራት በዋናነት ተከናውነዋል፡፡

በዚሁ መሠረት በፈቃድ ጠያቂዎች የሚቀርቡ የአካባቢና ማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናቶች መመርመር (Reviewing) እና ግብረ መልስ ማስጠት በቁጥር 68 ለማከናወን ታቅዶ በቁጥር 65 (የዕቅዱ 95.6%) ተከናውኗል፡፡ የነዳጅ ፍለጋና ልማት እና የማዕድን ልማት ፈቃድ ካላቸው ኩባንያዎች በሚገኘው ገንዘብ ሊሰሩ የሚቀርቡ የማህበረሰብ ልማት ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን ማምገምና ግብረ-መልስ ማስጠት በቁጥር 4 ለማከናወን ታቅዶ በቁጥር 3 (የዕቅዱን 75%) ተከናውኗል፡፡

እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተሰጡ ፈቃዶች ላይ አካባቢን በተመለከተ ባለፈቃዶች የገቡትን ግዴታዎች እየተወጡ መሆኑን በማስከ ክትትል ማድረግና ግብረ-መልስ ማስጠት እንዲሁም በፈቃድ ቦታዎች ላይ የሙያ ጤንነትና ደህንነት ክትትል ማድረግ በቁጥር 35 ፕሮጀክቶች ለማከናወን ታቅዶ በቁጥር 25(የዕቅዱ 71.4%) ፕሮጀክት ተከናውኗል፡፡

ከዘርፉ አልሚዎች የሚሟደብ የማህበረሰብ ልማት ገቢን ማስደግ በበጀት ዓመቱ ወስጥ ኩባንያዎች ከታቀደው በላይ በመክፈላቸው ብር 1,860,000 የተሰበሰበ ሲሆን የዘርፉ ልማት ለአየር ንብረት ለወጥ እንዳይበገር የኢኮኖሚ ግንባታ አሉታዊ ተጽዕኖ ቅነሳ እና ማላመጃ ፕሮጀክቶችን በመደገፍ በማዕድን ማውጣት ምክንያት የተጎዱ ቦታዎችን የአረንጓዴ ሽፋን 150 ሄክታር ለማከናወን ታቅዶ 96 ሄክታር (የዕቅዱን 64%) ተከናውኗል፡፡

የሥርዓተ-ፆታ ግንዛቤና ዕወቀትን በማጎልበት የአመለካከትና የአስተሳሰብ ለወጥ እንዲመጣ ለማድረግ እና በዘርፉ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማስደግ እንዲሁም የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ በዘርፉ ልማት እንዲካተትና ተግባራዊ እንዲሆን የክትትል እና የድጋፍ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ሠራተኞች እራሳቸውን ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እንዲከላከሉ የግንዛቤ ማስጨበጥ፣ ቫይረሱ በደማቸው ወስጥ ያለባቸውን የመንከባከብ እና በቫይረሱ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ የመ/ቤቱ ሠራተኛ ልጆች ክትትልና ድጋፍ የሚደረግ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

## 3. የአምስት ዓመቱን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማስካት የተሰሩ ሥራዎች

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመጀመሪያወን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን (2003-2007) ዕቅድ ለማስካት ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡ በልማት ዕቅዱ ዘመን በዕቅድ ከተያዙት በርካታ ሥራዎች ወስጥ የተወሰኑት በተለያዩ ምክንያቶች በዕቅዳቸው መሠረት ባይካሄዱም የአብዛኛዎቹ አፈጻጸም አጥጋቢ ነው፡፡ ይህንንም ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች ጋር በተደረገው ግምገማ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በልማት ዕቅዱ ዘመን በተከናወኑ ተግባራት የተገኙ አንኳር ወጤቶችን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የለወጥ ሠራዊት ግንባታን፣ የመደበኛና የካፒታል ፕሮጀክቶችን እና የክትትል፣ ግምገማ ግብረ-መልስ ስራዎችን በዕቅድ በመያዝ ተግባራዊ ያደረገ ሲሆን የለወጥ ሠራዊትን ከመገንባት አኳያ ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን የማስጠት እና መካከለኛ አመራሮችና ፈፃሚዎች ተፈራርመው በወሰዱት ግብና የግብ ማስኪያ አንኳር ተግባራት መሠረት ሥራዎች በዕወቀትና የጋራ መግባባት ላይ በመድረስ ተከናወነዋል፡፡

በዚህም መሠረት ባለፉት አምስት ዓመታት በ1፡250,000 ማስፈርት 354,000 ካሬ ኪሎ ሜትር በጂኦሎጂ እና በጂኦኬሚስትሪ፣ 390,490 ካ.ኪ.ሜ በሀይድሮጂኦሎጂ እና 216,584 ካ.ኪ.ሜ በጂኦሃዛርድ ጥናት ተሸፍኗል፡፡

በጂኦተርሚል ዝርዝር ጥናት **ቅድመ ጥልቅ የፍለጋ ጉድጓድ ቁፋሮ ጥናት የተጠናቀቀባቸውን** ቦታዎች **ሽፋን በ1:20,000 መስፈርት ወደ** 45% ለማሳደግ የተቻለ ሲሆን **በተንዳሆ የተገኘውን የመለስተኛ ጥልቀት 3 ሜጋ ዋት የእንፋሎት□ሃይል ጥናት በ2003 በጀት ዓመት 100%** በማጠናቀቅ ለልማት ዝግጁ ተደርጓል፡፡

**በዝርዝር የኢንዱስትሪ ማዕድናት ፍለጋና ክምችት ግምት በ1:50,000 መስ□ርትና በላይ 25** የአለኝታ ቦታዎች በጥናት የተከለሉ ሲሆን ዝርዝር የደለል ወርቅ ሜዕድናት ፍለጋና ክምችት ግምት በ1:2,000-1:5,000 ማስፈርት 22 አለኝታ ቦታዎች ተከልለዋል፡፡

**በድሪሊንግ ጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ 23560.35** ሜትር **□ኮር፣ □□ሃና □□ኦተርማል ቁ□ሮ** እንዲሁም በላብራቶሪ ስራ 202693 ናሙናዎች ምርመራ ለሰርቬዩና ለውጭ ተገልጋዮች አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን 20441 የጂኦሳይንስ መረጃዎች ተሰራጭተዋል፡፡

ለግሉ ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ከፍተኛ የካፒታል ማጠን ያስማዝገቡ ባለሀብቶች በሜዕድንና ፔትሮሊየም ፍለጋና ልማት እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት በ2002 የነበረው 12.7 ቢሊዮን ብር የሜዕድን ኢንቨስትመንት ማጠን በ2007 ወደ 32.592 ቢሊዮን ብር ያደገ በልማት ዕቅዱ ዘመን በተለያዩ የሜዕድን ዓይነቶች ላይ 191 የኢንቨስትመንት ፈቃዶች ተሰጥተዋል፡፡ በዚህም በአጠቃላይ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰጡ ፈቃዶች ቁጥር 239 ደርሷል፡፡ በሜዕድን ሥራ ላይ ከተሰማሩ ባለፈቃዶች ዓመታዊ ልዩ ልዩ ገቢ ብር 152.79 ሚሊዮን ተሰብስቧል፡፡

እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ 15 የፔትሮሊየም ፈቃዶችን እያስተዳደረ ሲሆን የኢንቨስትመንት ማጠኑም በ2007 ወደ 436.18 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር ማሳደግ ተችሏል፡፡ በ2002 ሜጨሻ 3.2 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የነበረው ከፔትሮሊየም ልዩ ልዩ ገቢ በአምስት ዓመቱ በደምሩ ብር 35.96 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ደርሷል፡፡

በልማት ዕቅዱ ዘመን በኩባንያዎች በኩል በድምሩ 20,726.46 ኪ.ግ ወርቅ፣ 516.97 ቶን ታንታለም እንዲሁም 2850.13 ሜኪብ ዕምነበረድ ለውጭ ገበያ ቀርቦ 831.78 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ተችሏል፡፡ እንዲሁም በባህላዊ አምራቾች በኩል 37,118.65 ኪ.ግ ወርቅ፣ 159,870.7 ኪ.ግ ጌጣጌጥ፣ 405.88 ቶን ታንታለም እንዲሁም 9.83 ኪ.ግ ፕላቲኒየም ለብሔራዊ ባንክና ለውጭ ገበያ ቀርቦ 1.79 ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት አምስት ዓመታት የውጭ ምንዛሪን ከማስደግ አኳያ በኩባንያዎችና በባህላዊ ማዕድን አምራቾች በኩል ተመርተው ለውጭ ገበያ ከቀረቡ ማዕድናት በድምሩ 2.62 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት ተችሏል፡፡

4. **ለህዳሴው ግድብ ግንባታ የመሥሪያ ቤቱና የሠራተኞች አስተዋጽኦ**

የማዕድን ሚኒስቴር ሠራተኞች የወር ደመወዛቸውን ለማስጠት በተስማሙበት መሠረት በመጀመሪያ ዙር በአጠቃላይ ብር436,657 በማዋጣት የቦንድ ግዥና ርክክብ ተካሂዷል፡፡ የሁለተኛው ዙርም ብር 435,499 በድምሩ 877.094 ተሰብስቦ ገቢ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች ዕድር ብር 50,000 እንዲሁም ከሠራተኞች ብድርና ቁጠባ ህብረት ሥራ ማህበር ብር100,000 ገቢ ሆኗል፡፡

በሌላ በኩል በማዕድን ዘርፍ ተሰማርተው የሚገኙ የብር፣የወርቅና ጌጣጌጥ ሰሪዎች ፣የጌጣጌጥ ማዕድናትና ታንታለም ላኪዎች፣ የሲሚንቶ ኩባንያዎች እና የወርቅ አቅራቢዎችን በማስተባበር የብር49,831,494.00 ቦንድ ግዥ እንዲፈፀም ተደርጎ በአጠቃላይ ብር50,634,362 ለግድቡ ግንባታ ገቢ ተደርጓል፡፡